# መንደሪ ነው አገሪ!

ወንድሜ ልጠይቅህ

ምኑ ቢታይህ ነው፤

እንዲህ የወሰንኸው?

በሰሜን፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እያለች፤

ለኔ ይበቃኛል ብለህ ማስታወቅህ

መንደሪ አገሪ ነች።

ጭራሹንም ሳትችል ዘመድህን ለመቁጠር

ቅድመ አያትህን አልፈህ፤

ወንድሜ ልጠይቅህ፣

ምን መጥቶብህ ይሆን አዋጅ ማስመታትህ፤

አገርነት ለኔ መንደሪ ይበቃል ብለህም መሟገትህ።

ላንተ መብት እንኳን አርቆ ለማሰብ ድንገት ካስቸገረህ

ወንደሜ ተገንዘብ፣ የሊሎቹን ምብት፤

አትተምን በበረት።

ደግሜም እላለሁ፣ ወንድሜ አዳምጠኝ ምንም ሳትበሳጭ

ዘምድህን ለመቁጠር ጭራሹንም ሳትችል

ቅድመ አያትህን አልፈህ፤

መብትህን አታጥብብ ማንም ቢያትልልህ፤

ኢትዮጵያን አሥትቶ

በክልል ምጣዱ እንጀራ ሲያሳይህ።

© ለምለም ፀጋው "ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ ቁ. 4" በ www.ethiomedia.com/ (http://www.ethiomedia.com/10parts/ydres_le_gonder_hizb.pdf) እትም

የተነሣሣ ና መንደሪ ለአገርነት ይበቃኛል ባይነት ለሚያስመስሉና የሌሎችንም መብት ለሚገድቡ ሁሉ መጠየቂያ፤ January 21, 2015